የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

ታሕሣሥ 27 ቀን 2011 ዓም

# ፋኖ

## <u>ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ</u>


የሕዝብ ግኑኝነት ተጠሪ ተሰማ ካሣ

ስ.ቁ 092705435

ስቅ 091349518

<u>ሱዳን፣ ካርቱም</u>


*ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ዛሬ እኛ የተረከብናትን አገራችንን ጠብቀው ያኖሯት ደማቸውን አፍሥሰው አጥንታቸውን ከስክሰው እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በኅብረት ጠላቱን ድባቅ ሊመታው የቻለው ኅብረትና አንድነት ስለነበረው ነው፣ ኅብረት የጥንካሬ ምልክት መሆኑን ያረጋገጡ አባቶቻችን በተግባር ለመላው ዓለም አሣይተዋል፣ ግዙፉ የአድዋ ጦርነት የዓለምን ፖለቲካ እንደቀየረ ዓለም የሚገነዘበው ነው፣ የድሉ ትቋዳሾች እኛ ብቻ ሣንሆን የዓለም ጭቁን ሕዝቦች የኮሩበትና ቅኝ ገዢዎች መላ ቅጡ የጠፋ አጀንዳቸውን እንዲፈትሹ ያስገደዳቸው ገድላችን ነው። ይህንን መቀበል የተሳነው ሕውሓት አኩሪ የአገራችንን ታሪክ ለመደምሰስ መማሰኑን በተጨባጭ የተረዳ ፋኖ ዱር በቴ ብሎ ወደ ዱር በመዝለቅ ወያኔንና ኢጋፋሪዎቹን በማንኮታኮት ወደ ጥንት ትውልዳቸው ቀጠና ወደ ትግራይ እንዲሸመጥጡ አስገድዷቸዋል። እነዚህ የወያኔ አመራር ወንጀለኞች በፈፀሙት ከባድ ወንጀል እንዳይጠየቁ ምሽግ ከትግራይ ተራሮች የቆፈሩ መስሏቸዋል፣ ግን ፍፁም እንደማይሆንላቸው ሣይታለም የተፈታ ገሃድ ነው።*

*ውድ ኢትዮጵያውያን*

*ወያኔ ከተፈጠረ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ እንቅልፍ ተኝቶ እንዳላደረ እንኳንስ እኛ የዓለም ሕዝብ የሚያውቀው ነው። ይህን ጋጠ ወጥ የሽፍታ መንጋ በቁጥጥር ሥር ካልዋለ*

ከኢትዮጵያ በዘረፈውና በመዘበረው ገንዘብ ቀደም በዘረጋው የቋንቋ ፌዴራሊዝም ጉዳት ማድረሱ እንደማይቀር የሰሞኑ ድርጊቶቹ አመላካቾች ሲሆኑ ይችላሉ።

ዛሬ ወገቡ እንደተሰበረ እባብ የሚሽመደመደው ወያኔ ያለፈው አልበቃ ብሎት በተባባሪዎቹ እሳት ጫሪንት በብዙ ቦታዎች አደጋ እያስጣለ ነው፡ ለአብነት ከሚጠቀሱት መካከል በወለጋ፣ በደቡብ ሕዝቦች፣ በባሌ፣በአርሲ፣በሐረር፣ በሸዋ፣ በራያ፣በቅማንት፣ወዘተ ጥቂቶች ሲሆኑ ከሁሉም የከፋ ደግሞ ተማሪዎች በተመደቡበት ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይከታተሉ በወያኔ ቅጥር ነፍሰገዳዮች እየተጠቁ ናቸው። የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ መንግሥትም ፍርሃት ይሁን ጭንቀት አቋሙ አልታወቀም፣ ሕዝባችን በአደባባይ ሲገደሉ ያለ ፍርድ ሲሰቀሉ ታሳሪ እንጂ አሣሪ የማይታወቅበት፣ ገዳማትና የአገር ቅርሶች የሚዘረፉበት ዘመን ላይ የደረስን ሲሆን ውርደቱን ለማምከን ፋኖ የአባት አደራን ለመወጣት ተሰማራ፣ ፋኖ የለውጡ ኃይል ሲሆን አነኳሱ ደሞክራሲን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማምጣት እንጂ ወለም ዘለም አልሸሹም ዞር አሉ የጥገና ለውጥ ለማጎናፀፍ አልነበረም። የወያኔን ሕገመንግሥት ወይም የጫካ ማኒፈስቶ መከታ በማድረግ የሚፎልሉ ወይም ፌዴራሊዝም አይለወጥም እሰጥ አገባ ብለው የሚሟገቱ በፋኖ ዘንድ ቦታ የላቸውም። በሌላም በኩል ደግሞ አንቀጽ 39 አይለወጥም ብለው የሚቃዡ ወስላቶች ከንቱ ባይባዝኑ እንደሚበጅ ፋኖ ይመክራል። የፋኖ አቋም በኢትዮጵያ ሕዝብ የተነደፈና የፀደቀ ሕገ መንግሥት በተግባር ተተርጉሞ ዴሞክራሲ በአገራችን እንዲሰፍን ነው። ፋኖ ኃላፊነት የሚሰማው መንግሥት በኢትዮጵያ እንድመሠረት በቆራጥነት እንደሚታገል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገልጽ ወያኔን የጡት አባት አድርገው የሚሞዳሞዱትን በጽኑ ይዋጋቸዋል። ፋኖ ኢትዮጵያ አገራችን ምንም ሣትሸራረፍ ለተተኪው ትዉልድ ለማስረከብ ቃል ኪዳኑን ስያድስ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪውን ሲያስተላልፍ አዲስ አባባ የኢዮጵያ ዋና መዲና መሆንዋን ያረጋግጣል። ፋኖ በኢትዮጵያዊነታቸው ከሚያምኑት ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት ዝግጁ ነው

EPNP

ድ ል ለ አ ን ድ ነ ታ ች ን ኢ ት ዮ ጵ ያ ለ ዘ ላ ል ም ት ኑ ር !!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

ኢሕብፓ

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY